# ፍጹም ታጋሽ ናት እማማ!

ሰርቶ መብላትም አቅቷት በወለደችው ታውራ!
በችጋር ደዌ መድይታ ድፍን አለምም እያማ፣
ካራውን ስሎ ገዝግዟት ገላዋን በደም በክላ፣
ብሩክ እንደ ወለደች እንደተነሳች ታርሳ፣
እሹ..ሩ..ሩ ትላለች እርጉም ባንቀልባ ሸክፋ፣
አንጀቷ ቁርጥ የማይል ፍጹም ታጋሽ ናት እማማ!

በእንስራ ውሃ አቅርባ እህሉን በመጅ ከክታ፣
ኩበት በቅርጫት ለቃቅማ ጭራሮ በእጇ ሰባብራ፣
ሶስት ጉልቾች ጎልታ ሰታቴ ምጣድ ዘርግታ፣
አይናማ እንጀራ ቀብታ እንጎቻውንም አንጉታ፣
እርሷ ሳትበላ ሳትጠጣ አንጀቷን አስራ በኩታ፣
“እደግ የኔ ልጅ!” እያለች እያጎረሰች አብልታ፣
ያሳደገችው ጣሮርዴ ጡቷን ቦጭቆ ጣላታ!

ከባእድ መንደር ተውሶ በቋንቋ ጩቤ ዘክዝኳት፣
የምታወርደው ሚሾና የሚፈስ እንባም ደርቆባት፣
እቅፍ አድርጋው ታድራለች እርሱ በጥርሱ ነግንጓት፣
ከአውሬዎች ብዙም ባይሻል የወለደ አይጥል ሆኖባት።

አምሳለ ገነት እያለ አምላክ በኤደን መስሏት፣
ከአባይ የወጣው ሙሴ እንኳን በመጻሕፍቱ ከትቧት፣
በደም የዋጇት ጴጥሮሷ አባት ቴዎፍሎስ ሞቶባት፣
በስመ-አብ ወ-ወልድ ሳይደግም የወለደችው ባረካት፣
አንገቷን በሐይል ቀንጥሶ ለማይሽር ሀመም ዳረጋት!

ካራውን ስሎ ገዝግዟት ገላዋን በደም በክላ፣
ብሩክ እንደ ወለደች እንደተነሳች ታርሳ፣
እሹ..ሩ..ሩ ትላለች እርጉም ባንቀልባ ሸክፋ፣
አንጀቷ ቁርጥ የማይል ፍጹም ታጋሽ ናት እማማ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ግንቦት ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.